ከሌይት ሰላም ዴሞክራሲ የሕዝብ መንግስት

## ~~ክፍል 1. መግቢያ~~ ለዘላለማዊት ሃገራችን ሰላም ዘላለማዊ ችግር እንዳይሆን

የኰለኔል መንግስቱ ኃይለማርያም አገዛዝ መውደቅ የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ሆኑ የዓለም አቀፍ ኰመኒቲ ለሃገራችን የተመኙትን የተሟላ ሰላምና አስተማማኝ ዲሞክራሲ ገና አላመጣለትም። እርግጥ ዛሬ የቀድሞው መንግስት መውደቂያ አከባቢ ለይ የነበሩት ኃይለኛ ግጭቶች የሉም። ግን ደግሞ ከየአቅጣጫው የሚቀጣጠሉ የጦር ግጭቶች ዛሬም አላቆሙም። የኢትዮጵያን ታሪክና ዛሬ ከፊቷ የተደቀኑባትን ውስብስብ ችግሮች ጠንቅቆ የሚረዳ ማንም ዜጋ ለሃገራችን ሰላምና ዲሞክራሲ በአንድ ቀን ለሊት ተሟልተውና ተስፋፍተው እንዲያድሩ አይጠብቅም። ይህንኑ ታሪክና የወቅቱን ችግሮች ልብ ብሎ የሚያጤን ዜጋ ደግሞ በዚያው ልክ እነዚህን የተሰበጣጠሩ ግጭቶችና የዲሞክራሲን አለመስፈን ከማንኛውም የሽግግር ዘመን የማይለዩ ቀለልና ሃለፊ ችግሮች አርጐ አይወስዳቸውም።

ለዘመናት የኢትዮጵያን ህዝቦች ፋታ ነስቷቸው የኖረው የሰላም መጥፋት እጅግ ሥር የሰደደ ታሪካዊና በህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ስነልቦናዊ ሥር መሠረቶች ያሉት ክስተት ነው። ግን ደግሞ ዛሬ የኢትዮጵያ ችግር ይህ ብቻ አይደለም። በረዥም ጊዜ የሰላም ማንበታ ጥረት እነዚህን ክስተቶች ህብረተሰቡ በቅጡ እንዳይዋጋ የሽግግሩ ዘመን ራሱ የወለዳቸው የፖለቲካ ችግሮች ማነቆ በመሆናቸው ዛሬ እነዚህን ቅርሶች በመዋጋት ፈንታ በነሱ እየተገፋን አገሪቱ ወደሌላ የጥፋት አዙሪት ልትወድቅ የምትችልበት አደገኛ ሁኔታ ለይ ትገኛለች።

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አንዴ በገዥዎቹ የጥቅም ግጭት፣ሌላ ጊዜ በብሔሮችና የጠቅላላው ህዝብ የህልውናና የመብት ተጋድሎ፣ሌላ ጊዜ ደግሞ የውጭ ወራሪዎችን ጥቃት ለመቋቋም በተካሄዱ ትንንቆች የተነሳ በልተቋረጡ የጦር ግጭቶች ለዘመናት ሲዋከብ የኖረ ህብረተሰብ ነው። በዚህ ጊዜና ታሪክ ተጋግዘው በጉዱት ህብረተሰባችን ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ የሰላም ፋታ፣ የዴሞክራሲና የማህበራዊ ፍትህ ፍንጭ ተነስተው ለዘመናት በመቆየታቸው ሃገራችንን የረሃብ፣ የስደት፣ የኋላ ቀርነትና የጭቆና ቋት እንደሆነች ለሁላችንም ግልፅ ነው። የዲሞክራሲ መጥፋት፣ ኋላ ቀርነት፣ የማህበራዊ ፍትህ መጓደል፣ የሚቀሰቅሷቸው ግጭቶች ድህነታችንን፣ ኋላ ቀርነታችንን፣ ጭቆናና ፍትህ አልበኑነትን እያበበሱ ይህ ደግሞ ሁኔታዎችን ለሌሎች ግጭቶችና ጦርነቶች እያመቻቸ ህብረተሰባችን እንደዚህ አውተብትበው እጅ ከወርች ከሰሩት የጥፋት አዙሪቶች ለማለቀቅ ፋታ ተነስቶ ሲዋከብ ለዘመናት ቆይቷል።

~~የእነዚህ የጥፋት አዙሪት መከማቸት የሚከሰተው በበሽታና በኢኮኖሚ ድቀታችን ብቻ አይደለም። በፖለቲከውም መስክ በሃገሪቱ ለሚከሰቱ ልዩነቶች ሁሉ ሌላ አማራጭ መፍትሄ ሳይፈለግ አመጽን የመጋበዝ፣ የፖለቲካ ተቃዋሚውን ሁሉ እንደደመኛ ጠላት መቁጠር፣ ትንሽ ለየት ያለን ሁሉ ከለየለት ተቃዋሚ ማምታታት፣ ልዩነት ማበማትን እንደጦር ከተት አዋጅ የማየት ባህል በህብረተሰባችን ስር ሰዷል።~~

ከዚህ አዙሪት ከጦር ድል ብቻ በተገኘ ማን አሀሉኝነት አይወጣም። በጊዜያዊ ወታደራዊ ድል ለይ ብቻ ተመርኩዞ ዘላቂ ሰላምን በተድበሰበሰ የፖለቲካ ሂደት ዲሞክራሲን መገንበት አይቻልም። የህብረተሰቡ አንድ ክፍል በአሸናፊነትና በበላይነት ሌላው ክፍል በመብት አልበኑነት ተቆለልፈው እስከተያዙ ድረስ ሁኔታዎችን ለቀጣይ ዙር ግጭቶችና አለመረጋጋት ማመቻቸት እንደሆነ የሩቁም ሆነ የቅርቡ ታሪካችን ያረጋገጠልን ሃቅ ነው።

የሽግግሩን ዘመን የፖለቲካ ስልጣን ከአንድ እጅ ወደሌላ የሚሸጋገርበት ጠባብ ሂደት አድርጎ መቀጠር ትልቅ ስህተት ነው።

አገራችንን እውተብትበው የያዟትን የጥፋት አዙሪቶች ለመስበር አስፈላጊ የሆኑትን ፖለቲካዊ፣ በህላዊና ሥነልበናዊ ለውጦች በውይይት ለማስወገድ የምንጀምርበትና እንዴ ከለፈ ደግሞ ለረዥም ጊዜ የማይመለስ ታሪካዊ አጋጣሚ መሆኑንም ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል ብለን እናምናለን። የሰላምና እርቅ አገር አቀፍ ጉባኤ ጥሪያችን የዚህ ግንዛቤ ውጤት ነው።

የሽግግሩ ሂደት ከፍ ተብለው የተጠቀሱትንና የሰላም ጠንቅ የሆኑትን ታሪካዊ፣ በህላዊና ስነልቡናዊ ክስተቶች የሚዋጋ ፖሊሲ በለመከተሉ ዛሬም እንደትናንቱ ኢትዮጵያ ወደሌላ የደም መፋሰስ ዙር እያመራች ትገኛለች።

ዛሬም እንደቀድሞው በወታደራዊ ኃይል በአሸናፊነት የወጣው ክፍል ይህንን ጊዜያዊ ድል ወደዘለቂ የፖለቲካ የበላይነት በኃይል ለመቀየር እየሞከረ ነው። በልዩ ልዩ ሽፋንም ቢሆን ዘር ዘር በአንድ ድርጅትና ለአንድ ድርጅት ጥቅም ብቻ ተረቶ የሚጸድቅ ህገመንግስት፣ በአንድ ድርጅት ቁጥጥር ሥር ለአንድ ድርጅት አሸናፊነት ተመቻችቶ የሚደረግ ምርጫ፣ ከዚህ ሁሉ ጋር ተያይዞ ተቃዋሚ ተብለው በሚጠረጠሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ የሚደረገው የመብት ረገጣ ዘመቻ፣ በዚህ ሁሉ ሂደት የማይስማሙ ኃይሎችን መሠረታዊ መብት ነፍጎ ከመሰሪያ ትግል ሌላ መውጫ ማሳጣት… እነዚህ ሁሉ አገሪቱን ወደጥፋት ይዘው የሚነጉዱ ክስተቶች ናቸው ብለን እንሰጋለን። ይህ የፖለቲካ ሁኔታና ዓላማ በሃቅ ለሰላም በሚደረግ ጥረት እስካልተቀየረ ድረስ ውስብስብ ችግሮቻችንን ከመፍታት ይልቅ እያባበስናቸው እንዳለፉት ዘመናት እነዚሁ ችግሮች ደግሞ የግጭቶች መነሽ እየሆኑ እንደገና ሌሎች የጥፋት አዙሪቶች ውስጥ እንዳንገባ መጠንቀቅ ከሁኑ ሊታሰብበት የሚገባው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

እንደማንኛውም ከረዥም ጊዜ ጦርነቶችና ግጭቶች እንደሚወጣና እነዚህ ደግሞ ከሚያስከትሉት ጥፋቶች ለማገገም እንደሚጥር ህብረተሰብ ኢትዮጵያም እጅግ ከበድና አጣዳፊ የሆኑ የመልሰ ማቋቋምና የመልሰመገንበት ተግባሮች አሉበት። በሃገሪቱ ላይ ከደረሰው ይህ ነው የማይባል የህይወት፣ የንብረት፣ የኢኮሎጅ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት ተቋሞች ጉዳት በተጨማሪ ከሁሉም ወገን በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ አካለ ስንኩላን፣ ባሎቻቸውን ያጡ ሴቶች፣ አሳዳጊ ያጡ ህፃናት፣ ጧሪ ያጡ ሽማግሎች አሉ። ያለአንዳች አድልዎና ማበላለጥ እነዚህን ሁሉ መልሰ ለማቋቋምና የኑሮ ተስፋ ለመስጠት መሞከር የማህበራዊ ፍትህ ጥያቄ ብቻ አይደለም። ለዘለቂ ሰላምም ሲባል የማይታለፍ አገራዊ ግዴታም ነው። በዚህ ላይ በጦርነቶችና በፖለቲካ ምክንያቶች በስደት የተፈናቀሉና በልተቋረጡ የርሃብ ዓመታት የተጎዱ ወገኖቻችንን አሁንም እገሌ ተእገሌ ሳንል በትግገዝ መንፈስ የመርዳትና የመልሰ ማቋቋም ተግባር አለብን። እነዚህን ሁሉ ስናይ በአንድ በኩል ከህብረተሰቡ እንክብካቤ የሚጠይቁ ክፍሎች ብዛት በሌላ በኩል ደግሞ ሃገሪቱ ለዚህ አቅርበት ያለትን እጅግ የመነመነ አቅም ስናስለ ያለፉትን ዘመናት የጥፋት ቅርሶች ለመቋቋም ብቻ ምን ያህል ከበድ ሃላፊነት በትከሻችን ላይ እንደወደቀ መገንዘብ ቀለል ነው።

ከሁለት ዓመት ወዲህ የሽግግሩ ሂደት በቀጠለቸው ወይም አዲስ በፈጠራቸው የፖለቲካና የጦር ግጭቶችና ሆን ተብለው በተወሰዱ የፖሊሲ ውሳኔዎች ሰቢያ

ከኑሩአቸውና ከአከባቢያቸው የተፈናቀሉ፣ የኑሮ ዋስትና ለራሳቸውም ለቤተሰባቸው ያጡ፣ ለስደት መከራ የተዳረጉ ዜጎች አሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩና ከህብረተሰቡ የማይናቅ ክፍል የሚወክሉትን እነዚህን ዜጎች የማይንከባከብና መልሰ ወደህብረተሰቡ ለማከተት የማይጥር ፖለቲካ አሁንም ከማህበራዊ ፍትህ የራቀ ፖለቲካ ብቻ አይደለም። ለሰላምና እርቅ ሂደታችን ውሎ አድሮ ከፍተኛ እንቅፋት ሊሆን የሚችል አደገኛም ፖለቲካ ነው።

በዚህ መልክ የቆዩ ከበድ ችግሮችን ሳይፈታ አዳዲስ ችግሮችን እየፈጠረ የሄደው የሽግግር ሂደት ከዘለቂ ሰላም ይልቅ አሸናፊዎች በህብረተሰቡ ላይ ለመጫን በሚሞክሩት ጊዜያዊ ጸጥታ ተዘናግቶና በዚህ ላይ ተመርኩዞ ህብረተሰቡ በሙሉ የሚያምንበት ዘለቂ ዲሞክራሲያዊ መድረክ ከመፍጠር ይልቅ አንድን ድርጅት ለስልጣን ለማብቃትና በስልጣን ለማቆየት ብቻ የተመቻቸ ወገናዊ ዲሞክራሲ ለማንገስ እየሞከረ ይገኛል።

በዚህም የተነሳ የመጋቢት ወሩ የፓሪስ ጉባኤ ተሰታፊዎች በሽግግሩ ሂደት ላይ የጠቆሟቸው አሉታዊና አደገኛ ክስተቶች ዛሬም ሳይታረሙ ወደ ዲሞክራሲና ሰላም የሚደረገውን ጉዞ እያደናቀፉት ይታያሉ። የሰብአዊ መብቶች አሁንም መረገጣቸውን እንደቀጠሉ በቅርቡ በጉንደርና በሐረርጌ ክፍለ ሃገራት የተከሄዱት ግድያዎች፣ በደቡብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች በህዝቡ ላይ በገፍ የሚደረገው ማሰደድና የእስራትና የግድያ ዘመቻ፣ የሰላሙን ጥሪ በመደገፋቸው በሽግግሩ ተሰታፊ በሆኑ ድርጅቶች ላይ የሚደረገው ዘመቻ፣ በሰበብ አስባቡ የጋዜጠኞችና የተለያዩ የፖለቲካ መሪዎች በእስር መንገላታት፣ የሙያ ማህበራትን አፍርሶ በታዛዥ ማህበራት ለመተካት የሚደረገው ጥረት፣ ሠራተኞችን ያለአንዳች ዋስትና ከስራ በማባረር ከነቤተሰባቸው ለእለት ጉርስ ችግር መዳረግ… እነዚህ ሁሉ ከፓሪሱ ጉባኤ ወዲህ እየተስፋፉ የመጡ ጸረ ሰላምና ጸረ ዲሞክራሲ ድርጊቶች ናቸው።

በፓሪሱ ጉባኤም ሆነ ከዚያም በፊት የሽግግሩ ሂደት የተሰከ እንዲሆን ሁሉም ይምከርበት፣ ሁሉም ይሰተፍበት የሚሉ ጥሪዎች ተደጋግመው ቢቀርቡም የሽግግሩ አመራር እንኳን ሌሎች ኃይሎችን ሊያስተባብር ቀርቶ እንዳንዴ ራሱ በማንአህሎኝነት ድርጅቶችን ሲያበርር ሌላ ጊዜ ደግሞ ድርጅቶች በዚሁ ማንአህሎኝነት በመመረር ራሳቸውን እያገለሉ ከመጋቢት ይልቅ ዛሬ የሽግግሩ ሂደት ይበልጥ የተራቆተበት ደረጃ ላይ ይገኛል።

የሰኔ ወር 1984 ዓም ምርጫ ኢትዮጵያውያንን እጅግ ያወዘገበና በበታው ተገኝተው የነበሩት ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በሙሉ ያጋለጡት መሆኑ እየታወቀ የሽግግሩ አመራር አሁንም ከዚህ ውድቀት ምንም ትምህርት የቀሰመ አይመስልም። በመሆኑም በዚያው በተለመደው የአሠራር ዘዴ የአንድን አገር የህጎች ሁሉ በላይ የሆነ ህገመንግስትን የመሰለ ቁምነገር እሱው አርቅቆ፣ ራሱ በወጣው የምርጫ ህግ አማከኝነት እሱው እንደራሴዎቹን አስመርጦ፣ ለማስጸደቅ የሚደረገው ሙከራ በምንም ዓይነት ለሃገሪቱ የተደለደለ ህጋዊ ሥርዓትም ሆነ ዘለቂ ሰላም እንደማያስገኝ ከሁኑ መተንበይ አስቸጋሪ አይሆንም።

ውለው እያደሩ የሚያድጉና የሚጉለብቱ የጦር ግጭቶችም ከመጋቢት ወዲህ ተስፋፉ እንጂ የመክሰም ፍንጭ አላሳዩም። በሃረርጌ፣በጉንደርና በሌሎች አከባቢዎች የሚከሄዱት የኢህአዴግ ሠራዊት ወታደራዊ ዘመቻዎች ለተቀናቃኞች ብቻ ሳይሆን ለሰላማዊ ዜጎች መጨፍጨፍ፣ ለመንበሮች መቃጠል፣ ለሃብትና ንብረት መውደም

ምክንያት ሆነዋል።

የፓሪሱ ጉባኤ የብሄሮችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ሙሉ በሙሉ አምኖና አረጋግጦ በሃገሪቱ አንድነት ጉዳይ ዋና ወሰኞቹ እራሳቸው የሃገሪቱ ህዝቦች እንጂ እንዳለፉት ዘመናት ምንም ህዝባዊ መሠረት ሳይኖራቸው ከራሳቸው አልፈው መጭ ትውልዶችን በልዩ ልዩ ገዴታዎች ውስጥ ለመጨመር በሚጥሩ መንግስታት እንዳልሆነ ያለውን እምነት ገልጧል። ከዚያ ወዲህ በኤርትራ ሬፈራንደም ተከሂዶ የኤርትራ ነፃነት ታውጇል።

በሌላ በኩል የሃገሪቱን መስተዳድር፣ ኢኮኖሚዋን፣ የዜጉቿን መብት፣ የመከለከያና የፀጥታ ተቋሞቿን፣ እንዲሁም በውጭ ግንኙነት ዓለም አቀፋዊ ሀልውናዋንና ፖሊሲዋን የሚመለከቱ ይፋና ስውር ውሎች መፈረማቸው እነዚህ ሁሉ ገና በሰላምና በዲሞክራሲያዊ ውይይት መፍትሄ የሚያስፈልጋቸው ውዝግቦች ፈጥረዋል።

በቻርተሩ በራሱ ታውቆ የነበረው የብሄሮች መብት እንደማንኛውም ሌላ የቻርተሩ አንቀጽ በኢህአዴግ ፀረ ዲሞክራሲያዊ አሠራር ምክንያት ከስራ ላይ ሊውል አልቻለም። በዚህ የተነሳ ብሄሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰንና በዲሞክራሲያዊ ምርጫ አማካኝነት የራሳቸውን አስተዳደር መመሥረትም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ አልቻሉም። ከዚህም አልፎ በየክልሉ በቀድሞዎቹ አገዛዞች የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ኢህአዴግ በፈጠራቸው የብሔር ድርጅቶች አማካኝነት ህብረተሰቡ እርስ በእርስ እንዲቃረንና እንዲበጣበጥ እየተደረገ ነው።

እነዚህ ሁሉ የሽግግሩን ወቅት አሰራር ዘዴዎች ፀረ ዲሞክራሲያዊነት ከእለት እለት በይበልጥ እያከሄዱ ሃገሪቱንም ለተጨማሪ ውዝግቦች የሚዳርጉ እንጂ የሚያስፈልጋትን ሰላምና እርቅ የሚጋብዙ አይደሉም።

መጋቢት ላይ የነበሩ ችግሮች፣ ያኔ የተጠቆሙ የሰላማዊ ሽግግራችን ጠንቆች እነሆ በዚህ መልክ ተበበሱ እንጂ እየተቃለሉ አልሄዱም። የፓሪሱ ጥሪ አነሳሾች ዛሬ ሃገሪቱ ያለባት ችግሮች ቀላል እንዳልሆኑና እጅግ የተወሳሰቡ እንደሆኑ ያኔም አልሟቷቸውም እንዲያውም አገር አቀፍ የሰላምና የእርቅ ጉባኤ ተደርጐ ሁሉም ሃለፊነት በተመለበት መንፈስ ከጊዜያዊ የቡድንና የፖለቲካ ጥቅም በሸገር ስለዘለቂ ሰላም ሁሉን ያከተተ ወይይት ይደረግ ብለው ጥሪ ሲያደርጉ መነሻ ያደረጉበት ነጥብ ነገሮች እጅግ ከመወሳሰባቸው የተነሳ በጥሞና ከሚከሄድ ውይይት ሌላ የተሻለ መፍትሔ አይኖርም ብለው በማመናቸው ነበር።

ኢህአዴግና የዚህ ድርጅት ደጋፊ የሆኑ ሀይሎች ይህንን አለመገንዘባቸውና ከሰላሙ ጥረት ራሳቸውን ማገለላቸው እጅግ አሳሳቢ የሚሆነው እዚህ ላይ ነው። ከመጋቢት እስከሁን እየተባበሱ የመጡት ችግሮች ይህ አገር አቀፍ ውይይት እስከልተከሄደ ድረስ በመጭውም ጊዜ እየተባበሱ እንጅ በምንም ተአምር እየከሰሙ አይሄዱም። ኢህአዴግ ከዚህ ሂደት ራሱን አግልሎ ወደዘለቂና ቋሚ መንግስት ለማሸጋገር የሚየደርገው ጥረት በቀጠለ ቁጥር ጸረ ዲሞክራቲክ አሰራሩ እየተፋፋመ፣ ይህ ደግሞ ይበልጥ ተቃውሞን እየቀሰቀሰበት፣ ይህንንም ለማቷቷም ጸረ ዲሞክራትነቱንና ጸረ ሰላም እርምጃዎችን እያበራከተ የሚሄድበት አዙሪት ውስጥ ራሱን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን ይዞ የሚነጉድበት ሁኔታ ይፈጠራል ብለን እንሰጋለን።

ይህ አስጊ ሂደት እንደ ሱማሊያ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁኔታ እንዳይፈጠርና ያለፉት ዘመናት መከራዎች አንሰው ሃገሪቱ ወደሌላ የትርምስ ዙር እንዳትገባ የተቻለውን ሁሉ መጣር የዜጎች ሁሉ አጣዳፊ ተግባር ነው። ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት የሽግግሩ ሂደት ያስጋቸው ሀይሎች እንዲታረሙ የሚጠቁሟቸውን ጉድለቶች ብቻ ሳይሆን ያለቸውን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ አማራጭ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ሆነ የሃገሪቱ ሁኔታ ለሳሰበቸው በአዳን ወደጆች አቅርበው ወግና ስነ ስርአት ያለው ውይይትና የፖለቲከ ትግል ማከሄድ ይኖርበቸዋል። የዚህ ጉበኤያችን መሰረታዊ አለማም ይኸው ነው።

NATIONAL CONFERENCE FOR PEACE AND RECONCILIATION IN ETHIOPIA
CO ORDINATING COMMITTEE
ለሰላምና ዕርቅ በኢትዮጵያ
አገር አቀፍ ጉባኤ አስተባባሪ ኮሚቴ
CONFERENCE NATIONALE POUR LA PAIX ET LA RECONCILIATION EN ETHIOPIE
COMITE DE COORDINATION